በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡209319

ቀን፡28/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አብደላ ከሊል - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - ኤጀታ ሓተኡ- ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) እና አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 2(10) ፤22(10) እና 50(ለ)(1) ን በመጥቀስ ባቀረበው ክስ ጥር 05 ቀን 2013 ዓም ከቀኑ 3፡00 በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 08 ውስጥ በሚገኘው ለተጨማሪ እሴት ታክስ

በተመሰገበው የህንፃ መሳሪያ መሸጫ ድርጅት ባለቤትና አስተናጋጅ ሆነው ሲሰሩ ብረት የሚታሰርበት ፒንሳ በብር 130.00 ለዐቃቤ ህግ ምስክሮች ሲሸጡ ወዲያውኑ ደረሰኝ ሊሰጡ ሲገባ ያለደረሰኝ ግብይት ፈፅመዋል በማለት ከሷል፡፡

አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክሱን ክደው ስለተከራከሩ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው የተሰሙ ሲሆን ምሰክሮቹም በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜና ቦታ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነ የህንፃ መሳሪያ መሸጫ ሱቅ ውስጥ አመልካች አስተናጋጅ ሆነው እየሰሩ ፒንሳ በብር 130.00 ገዝተው ገንዘቡን ከፍለው እቃውን የተረከቡ ቢሆንም አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልሰጧቸው መሆኑን ስላስረዱ ፤ይህንን የምስክርነት ቃል ከሰነድ ማስረጃዎቹ ጋር መርምሮ አመልካች እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቶ አመልካች ሁለት ምስክሮችን አቅርበው በእለቱ ሽያጩ ተከናወነ በተባለበት ስፍራ ያልነበሩ መሆኑን ከዚህ ይልቅ ጀሞ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት ከዚያም ወደ ቃሊቲ በመሄድ እስከ 6፡30 ድረስ የዋሉ መሆኑን ያስረዱ ቢሆንም 1ኛ የመ/ምስክር አመልካች ከነሱ ጋር የነበረው ከጠዋቱ 2፡00 ጀምሮ ነው ሲል 2ኛ የመ/ምስክር ከ2፡40 ጀምሮ ነው ማለቱ መሰረታዊ ልዩነት ያለው በመሆኑ የምስክርነት ቃሉ እምነት የማይጣልበት መሆኑን ፤አመልካች በስራ አስኪያጅነት ጭምር የተከሰሱ በመሆኑ በስፍራው አለመኖራቸውን ማስረዳታቸውም ቢሆን ከወንጀል ሀላፊነት ሊያስመልጣቸው የማይችል መሆኑን በመጥቀስ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ በማለት በአንድ አመት ቀላል እስራትና በብር 3,000.00 እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን ይህ ውሳኔም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በክሱ ላይ ተጠቅሶ የወንጀል ክስ የቀረበብኝ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 138 መሰረት ተፈፃሚነቱ ያበቃ ሆኖ እያለ በተሻረ ህግ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤አዋጅ ቁጥር 609/2001 አዋጅ ቁጥር 285/1994 ን ያሻሻለ ሆኖ ሶስት አንቀፆችን ብቻ የያዘ ሆኖ እያለ አንቀፅ 22 እና 50 እንዳለው በመውሰድ በሌለ ድንጋጌ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም፤የስር ፍርድ ቤት ስራ አስኪያጅ ሳልሆን ከአዋጅ ቁ.983/2008 አንቀፅ 2(19) ትርጉም በመውጣት ስራ አስኪያጅ ነህ በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው፤የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ያደሩበትን ቦታ፤አመልካች የተያዝኩበትን ጊዜ አስመልክቶ ልዩነት ያለው የምስክርነት ቃል ሰጥተው እያለ ፤ምስክሮቹ ሽያጩ ተከናወነ ያሉት በ05/05/2013 ዓም ሆኖ እያለ ቃሌን ለፖሊስ የሰጠሁት ደግሞ በ04/05/2013 ዓም ሽጠሃል ተብዬ ሆኖ እያለ በአጠራጣሪ ማስረጃ ይህንን አጠራጣ ማስረጃም የመከላከያ ምስክሮቹ ባስተባበለ መልኩ አስረድተው እያለ የጥፋኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰጠቱ አግባብ አይደለም፤

የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን የሰጠው ማስረጃዎቼን በአግባቡ ሳያስቀርብ የመከላከል መብቴን በማጣበብ በሰ/መ/ቁ.139107 እና 95921 የተሰጡትን አስገዳጅ ውሳኔዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ከላይ

በተመለከተው አግባብ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሊሻር እና በነፃ ልሰናበት ይገባል፤ይህ ቢታለፍብኝ በመኪና አደጋ ምክንያት ያለብኝ የዲስክ እና የነርቭ በሽታ ከግምት ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ ሊገደብልኝ ሲገባ የስር ፍርድ ቤት ይህንን በማለፍ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ የእስራት ቅጣቱ ሊገደብልኝ ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች የጤና ችግር ያለባቸው ስለመሆኑ ከሆስፒታሎች ማስረጃ ቀርቦ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን ሳይገድቡ ያለፉበትን አግባብ በሰ/መ/ቁ.48956 እና85596 ከተሰጡት አስገዳጅ ውሳኔዎች አንፃር ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መልሱን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ  በሰጠው መልስም አመልካች ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማከናወኑን በመጥቀስ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን አዋጅ ቁጥር 285/94 እና 609/2001 በመጥቀስ ክሱ መቅረቡ በአግባቡ ስለሆነ አዋጅ ቁጥር 983/2008 የታክስ አስተዳደርን የሚመለከት አጠቃላይ አዋጅ በመሆኑ ይህ አዋጅም ክስ የቀረበባቸውን አዋጆች በግልፅ ያልሻረ በመሆኑ አመልካች በዚህ አግባብ ያቀረቡት ክርክር ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ማስረጃ ምዘናን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የቀረበለትን ማስረጃ ያገናዘበው በሰ/መ/ቁ.89676 በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አግባብ በመሆኑ ገደብን አስመልክቶም አመልካች በጠቀሷቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች አግባብ እልባት የተሰጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን አላቀረቡም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡በመሰረቱ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን ሰምተው በመመርመርና በመመዘን የሚደርሱበት መደምደሚያ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠን መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን ብቻ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እና በህገ መንግስታችን አንቀፅ 80(3)(ሀ) በተሰጠው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረም አይደለም፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይም የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው የተጠሪ ምስክሮች ንብረትነቱ የአመልካች በሆነ የህንፃ መሳሪያ መሸጫ ሱቅ ውስጥ አመልካች አስተናጋጅ ሆነው እየሰሩ ፒንሳ በብር 130.00 ገዝተው ገንዘቡን ከፍለው እቃውን የተረከቡ ቢሆንም አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልሰጧቸው መሆኑን ሲያስረዱ የአመልካች መከለከያ ምስክሮች አመልካች ሽያጭ ተከነወነ በተበለበት ወቅት በስፍራው አለመኖራቸውን በሚያሳምንና ልዩነት በሌለው መልኩ አለማስረዳታቸውን በመጥቀስ ነው፡፡የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን በመስማት በመመርመርና በመመዘን በፍሬ ነገሮች ላይ የደረሱበት ድምዳሜ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማረም ስልጣን ብቻ በተሰጠው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረም ሆኖ ስላላገኘነው አመልካች በፍሬ ነገር ጉዳይ ክርክር ላይ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በተመለከተም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበትን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙት ጥር 05 ቀን 2013 ዓም ሆኖ እያለ ተጠሪ ድርጊቱ ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ አንፃር ተግባራዊ አፈፃፀም ያለውን የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 131(1)(ለ) በመጥቀስ ክሱን ሊያቀርብ ሲገባ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) እና አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 2(10)፣22(10) እና 50(ለ)(1) ን በመጥቀስ ክሱን ማቅረቡና የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንን ስህተት በማረም ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ሊሰጡ ሲገባ አመልካችን አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) እና አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 2(10)፣22(10) እና 50(ለ)(1) ን በመጥቀስ ጥፋተኛ ማለታቸውና የቅጣት ውሳኔውንም በዚሁ ድንጋጌ ስር መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በአመልካች ላይ ከሚጣለው የእስራት ቅጣት አንፃር በሁለቱ ድንጋጌዎች መሃል ልዩነት ባለመኖሩ አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 131(1)(ለ) ስር ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡

የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ በተባሉበት የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 131(1)(ለ) የገንዘብ መቀጮ ከእስራት ቅጣቱ በተጨማሪ ያልተመለከተ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ አመልካች ብር 3,000.00 እንዲቀጡ የሰጡት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ገደብን አስመልክቶ አመልካች ለገደብ ጥያቄያቸው መሰረት ያደረጉት የህክምና ማስረጃ የዲስክ መንሸራተት ህመም ያለባቸው መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር አመልካች ባለባቸው ከፍተኛ የጤና ችግር ምክንያት በማረሚያ ቤት ሊቆዩ የሚችሉበት አግባብ ሁኔታ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ባለመሆኑ ከዚህ የተለየ እና የእስራት ቅጣቱን ለመገደብ የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ከተገቢው ማስረጃ ጋር ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለማያሳይ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በፊንፊኔ ዙርያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.72079 ሚያዝያ 14 ቀን 2013 ዓም የሰጠው የጥፋተኝነት እና ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የኦ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.350497 ግንቦት 12 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 131(1)(ለ) ስር ሊሆን ይገባል፣ በዚህ አግባብም ብር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3,000.00 እንዲቀጡ በስር ፍርድ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ከዚህ ውጪ ያለው የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ፀንቷል፡፡

2. ጉዳዩ ውሳኔ እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም